# የነፃነት ሃውልት



ኢትዮጵያን አቁሞ፣ ለኛ የተሰዋልን፣

ሕይወት የከፈለ ፣ አገር ያቆመልን፣

አምቢ አሻፈረኝ ፣ ብሎ በቆረጠ፣

ደረቱን ለጥይት ፣ ለሃገሩ በሰጠ፣

ፋሽስትን አዋርዶ ፣ አንገቱን ባስደፋ፣

የሕዝብ ኩራት ሆኖ ፣ ለኛ በተደፋ፣

የፈርሳል ይሉናል ፣ የነፃነት ሃውልት፣

በደም የተሰራ ፣ ጠላት ያፈረበት!!

ነፃነቴን ወስዶ ፣ ታሪኬን የሚያፈርስ፣

ባንዲራ ነፃነት ፣ አይደለም ወይ ጴጥሮስ!!

ማነው ቃታ የሳበው ፣ ጥይት የተኮሰው፣

ባንዳ የባንዳ ልጅ ፣ አይደለም ወይ ያሰው!!

እረኛኙ አያቱ ፣ እሱ ሃውልት አፍራሽ፣

የግራዚያኒ አሽከር ፣ ሕዝቡን አስለቃሽ፣

ጉዱን ለመሸፈን ፣ ሚስጥር እንዲደበቅ፣

ትውልድ እንዳያውቀው ፣ ስራው እንዳይታወቅ፣

ይፈርሳል ይሉናል ፣ የነፃነት ሃውልት፣

በደም የተሰራ ፣ ጠላት ያፈረበት!!

እንቢልታ ይነፋ ፣ የነገረው ሕዝቡ፣

ባርነትን እምቢ ፣ ነፃነት ነው ግቡ፣

ማዕበል ነው እሱ ፣ ከሩቁ የሚያስፈራ፣

ኃያል ነው ጴጥሮስ ፣ አሞተ ኮስታራ፣

ለሃገር የነደዱ ፣ እሳት ነበልባሎች፣

ታሪክ የሚደግሙ ፣ ጠላት አርበድባጆች፣

ብዙ ልጆች አሉት ፣ እንደሱ እሚሞቱ፣

እስቲ ሞክሩታ ፣ ተጠጉ ከሃውልቱ፣

ሃውልቱ ይኖራል ፣ ሁሌም እንዳበራ፣

እሳት ነው ይፋጃል ፣ በደም የተሰራ፣



የነፃነት ኀህ ነው ፣ የፀሃይ ውጋጋን፣

ሻማ ነው ፣ ብርሃን ለኛ የነደደልን።

ፈረስ ያለ ልጓም ፣ ይወጣል ወይ ደጅ፣

አንተ የመሰለኒ ፣ የፋሽስት ወዳጅ፣

ጎባጣ ነህ አሉ ፣ ጨርሶ የማትቀና፣

አንተ አምቧታሪ ፣ ደፋታ ነህና፣

ዳግመኛ ብትመጣ ፣ መልክህን ቀይረህ፣

ሉሲፈር ታውቀሃል ፣ ድባቅ ትመታለህ፣

አንተ ሊሬ ለምደህ ፣ እንደ አያቶችህ፣

ፍርፋሪ መልቀም ፣ ለከርሱ አዳሪ፣

ስብዕና የሌለህ ፣ ወገን አሳፋሪ ።

ድልማ ሁልግዜ ፣ የኛ አይደለም ወይ፣

እኔን የሚገርመኝ ፣ ለቃቃሚ ሳይ!!

በሕበረት እንቁም ፣ ከጎኑ ፣ እንሰለፍ፣

ሃውልቱ አይፈርስም ፣ ሕይወታችን ትለፍ!!

ሃውልቱ አይፈርስም ፣ ሕይወታችን ትለፍ!!



ጴጥሮስ ሐውልት ሲቆም የበዓሉ አከባበር

መይሳው ከምድረ ስዊድን 2012-12-03